Solomon Yohannes
0911060113

# መጽሐፈ ምሥጢር

# መጽሔት

አ ሚ ን ።

(ሀ) የኦርቶዶክስን ሃይማኖት ባህልና ታሪክ አምስቱን አዕማደ ምሥጢር ፤
(ለ) በዓለም ውስጥ የሚገኙትን የሃይማኖትን ስልቶችና ባህላቸውን ፤
(ሐ) ከኒቅያ ጉባኤ ገሮምሮ ስለ ሃይማኖት የተሰበሰቡት ስምንቱ ጉባኤዎችን ።
(መ) የኢትዮጵያን ነገሥታት ተራ ቍጥርና አጭር ታሪክ ፤
(ሠ) በኢትዮጵያ የተሾሙትን ጳጳሳትና የእጨጌዎችን ተራ ቍጥር የሚያሳይ ።

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

ከአክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ

ተዘጋጀ

ተጎትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ወ፱ቱ ዓመተ መንግሥቱ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

ወበራብዕ ዓመተ ሢመተ ሊቀ ጵጵስናሁ ለብፁዕ አባ ባስልዮስ
ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ።

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፶፩ ዓ. ም.

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ፰ ፴፯ ቀ ፳፻፴፬ መ ፫ሺ


ዋጋው ፪ ብር ከ፶ ሳንቲም ።

www.ethiopianorthodox.org

D.N Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609

ያለ ደራሲው ፈቃድ ገልብጦ ማሳተም ክልክል ነው ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
Solomon Yohannes
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም ።

### የመጀመሪያውን ስፍራ የእምነት ታሪክ ሊይዘው ይገባል

### ወንድሜ ሆይ ።

ከፈጣሪው አብልጠ የዓለምን ከንቱነት የሚወድ ሰው ሁሉ ለጣዖት የሚሰግድ አረማዊን ይመስላል ። የሚገባንን ሥራ ሁሉ ስንሠራ ፍጻሜውን ለእግዚአብሔር መተው ይገባናል ። እርሱም ሕጉንና ትእዛዙን የሚጠብቀውን ሁሉ እንዳይበደል ይጠባበቃል ። የሰውነት ተፈጥሮ ያዘጋጀውን እንሠራለን በማለት ፤ የተፈቀደውን ደንብና ሕግ ስንጥስ ከአዋቂው መሪያችን ከእግዚአብሔር እጅ መውጣታችን ነው ። በዚህም ምክንያት ለሚደርሰው ሁሉ ነገር እኛው ራሳችን ኃላፊው ነን ። ደግሞ ሐሳባችንን በደንበኛው መንገድ ለመፈጸም የተነሣን እንደሆነ ለጊዜው ሥራችን ባይያዝ ስንኳን ፤ ወደፊት ዋጋችንን እናገኛለን የማለት ተስፋ ማድረግ ይገባናል ።

### መ ገ መ ሪ ያ ።

አዳምና ሔዋን ከተከለከለው የዛፍ ፍሬ ከበሉ በኋላ የኃፍረትና የፍርሃት ዕውቀት ሞላባቸው ። የመገመሪያውም ሐሳባቸው ለኃጢአታቸው ምክንያት ፈጥረው ከሚያስፈራው ከሞት ፍርድ ለመዳን ብቻ ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለኃጢአታቸው በጠየቃቸው ጊዜ ፤ አዳም ኃጢአቱን በእግዚአብሔርና በባልንጀራው በሔዋን ላይ አመካኘ ። እንዲህ ሲል ። ከእኔ ጋር ትሆን ዘንድ የሰጠኸኝ ሴት ፤ እርሷ ከዛፉ ፍሬ ሰጠችኝና በላሁ አለ ። ሴቲቱም ነውሯን በእባቢቱ ላይ አመካኘች ። እንዲህ ስትል ። እባቢቱ አታለለችኝና በላሁ አለችው ። እንዲህም ማለትዋ ስለምን እባቢቱን ፈጠርህ ፤ ወደገነትስ ትገባ ዘንድ ለምን ፈቀድህላት ማለቷ ነው ። ይህንንም ማለቷ ራሷን የማጽደቅና የማታለል መንፈስ ስለ አደረባት ነው ። ይህም ማታለል በሐሰት አባት በሰይጣን ተገመረ ። ቀጥሎም በአዳምና በልጆቹ ላይ ተገለጸ ። ይህም የማታለል መንፈስና ሥራ ሁሉ የሰይጣን ክፍል ነው ።

እውነተኛ መንፈስ ግን በኃጢአትም ተሰናክለን ብንወድቅ በንስሐ ተጽናንተን እንድንነሣ ይረዳናል እንጂ ወደ ማታለል ሥራ አይመራንም ። እነሆ እውነተኛው መንፈስ ያደረበት ያምስኪን ቀራጭ ስለ ኃጢአቱ እንዲህ ሲል ጮኸ ። አቤቱ እኔን ኃጢአተኛውን ይቅር በለኝ ብሎ ተናገረ ዓይኑን ስንኳ ወደ ሰማይ ለማንሳት ሳይደፍር ኃጢአቱን ለፈጣሪው አስታወቀ ።

### አሁን የተነሣንበት ክፍል ።

የዘመናዊው ትምህርት ቤት ወጣቶች በታላላቅ ትምህርት ላይ የሚገኙ ሁሉ ስለ ሀገራቸው ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እምነቷና ታሪኳ ምን ጊዜ እንደ ተገመረና የእምነታችንም አኳኋን ምን ዓይነት እንደ ሆነ ሁል ጊዜ በምናስተምርበት ክፍል እየ

www.ethiopianorthodox.org

